## 3. ተውሂድ አል-አስማኡላሂ ወሲፋቲሂ( በአላህ ሰሞችና ባህሪያት ማመን)

ይህ የተውሂድ ክፍል በአላህ ባህሪያትና ስሞች ማመን ነው። አላህ ሱ.ወ በቁርአኑ ውስጥና በመልክተኛው (ሰ ዐ ወ) አንደበት ራሱን በገለጸበት እና በሰየሙበት ስምና ባህሪያት ለራሱ ለአላህ ብቻ ማድርግ ነው። ይህ ማለት አላህ ሱ.ወ ወይም መልእክተኛው (ሰዐወ) በገለፁበት መልኩ ያለምንም መቀነስና መጨመር እንዲሁም ያለ ምንም ማመሳስል በተገለፀበት መልኩ መቀበልና ማመን ማለት ነው። ሲፋቱን( ባህሪውን ) ከፍጡር ጋር ማመሳሰል፤ ወይም ማሳጣት የዚህን የተውሂድ ክፍል የሚቃረኑ ነግሮች ናቸው። አላህም እንዲህ ይላል..

### "......እሱን የሚመስል ምንም ነገር የለም እሱ ሰሚና ተመልካች ነው" (ሹራ፤፲፩)

በዚህ አያ ላይ አላህ ሱ.ወ እሱን የሚመስል ማንም እንደሌለ እየነገረን ተመልካችና ሰሚ እንደሆነም ነግሮናል ። ይህ ማለት አላህ ከፍጡራኞች በተለየ መልኩ እንደሚያይ እና እንደሚሰማ አምኖ መቀበል ነው።

የአላህን ሱ.ወ ባህሪ በኛ ውስንና ጠባብ በሆነው የመገንዘብና የማሰብ ችሎታችን ልንደርስበት የማንችል ፍጹም የመጠቀና የተቀደሰ መሆኑን ከልብ መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

"ጅንና ሰውንም እንዲገዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።" (አዛሪያት

## የዳእዋ እንቅስቃሴዎች፤

- **ሳምንታዊ የዳእዋ ዝግጅት**

ኢትዮጵያዊያን ሙስሊም እህቶችን

ኢስላማዊ እውቀትን እንዲያዳብሩ

በቋንቋቸው የተዘጋጀ መድረክ

ዘወትር **ሃሙስ 10:00pm EST**

በስልክ ቁጥር፡

**218-862-7200 ወይም 219-509-8111**

መግቢያ ቁጥር (Bridge #) ፡ **585149**

- **ማስ ኢሜል ግሩፕ (Mass Email Group)**

ሳምንታዊ የሃዲስ እና የዳእዋ

ማስታወሻዎችን እያንዳንዱ ሰው ባለበት

በቀላሉ በኢሜል ለማስተላለፍ የተመሰረተ

ኢሜል አድራሻዎቻችሁን በመላክ የዚህ የተቀደሰ

ስብስብ አባል ይሆኑ ዘንድ በትህትና እንጋብዛችኋለን።

Muslimah@badrethiopia.org

**(ለሴቶች እህቶችቻችን ብቻ የተዘጋጁ ፕሮግራሞች)**

# ተውሂድ

**በበድር የሴቶች ዳእዋ ግሩፕ ተዘጋጅቶ የቀረበ**

# ተውሂድ (አሏህን በአምልኮት መነጠል)

**“(እርሱ)፡ የሰማያትና፡ የምድር፡ በሁለቱም መካከል ላለው ሁሉ ጌታ ነውና ተገዛው፡ እርሱም መገዛት ላይ ታገስ፡ ለእሱ ሞክሼም ታውቃለህን?” (መርየም 65)**

አሏህ እሱን ለማምለክ ለበጎ ስራና ላላማ ፈጥሮናል። ለዚህም ሲል በየጊዜው መልእክተኞችን ተውሂድ እንዲያስተምሩ ሰዎችን ወደ “ኢኽላስ” እንዲጠሩ በየዘመናቱ ልኳል። ተውሂድ ማለት አላህን በብቸኝነት መገዛት ማለት ነው። (የማጋራት ተቃራኒ) ተውሂድ እጅግ ሰፊና ምሉዐ እና ውብ ማራኪ ነው። አላህ ሱ.ወ ተውሂድን እንደ ሰማይ መስሎታል፤ ተውሂድን የተወን ሰው ደግሞ ከሰማይ ወደ መሬት እየተምዘገዘገ በሚወድቅ ነገር መስሎታል። ምክንያቱም ከኢማን ምጥቀት ወደ ኩፍር ዝቅጠት እያሽቆለቆለ ነውና።

አብዛኞቹ የእውቀት ባለቤቶች ተውሂድን በሶስት ይከፍሉታል፤

-ተውሂድ አር-ሩቡቢያ ( የጌትነት አምልኮት)

-ተውሂድ አል-ኡሉሁያ ( አምልኮታዊ ኢባዳ)

-ተውሂድ አስማኡላሂ ወሲፋቲሂ (የአላህ ስሞችና ባህሪያት አምልኮ)

1. ተውሂድ አር-ሩቡቢያ ( የጌትነት አምልኮ)

በመፍጠር በልዕልና እና በማስተናበር አላህን ብቸኛ ማድረግ ነው። በመፍጠር ረገድ አላህ ብቸኛ ፈጣሪ መሆኑን ማመን ነው፡ ከአላህ ሌላ ፈጣሪ አለመኖሩን ማመንና መቀበል ነው። አላህም እንዲህ ይላል

**“... ከሰማይና ከምድርም ሲሳይን የሚሰጣቸው የሆነ ከአላህ ሌላ ፈጣሪ አለን? ከርሱ በስተቀር አምላክ የለም ...” ፋጢር 35:3**

የአንድ ነገር ፈጣሪ የባህሪውም ፈጣሪ ነው። በሌላ በኩል ሲታይ ደግሞ የሰው ስራ የተገኘው በሰውየው ቁርጠኛ ፍላጎት ሙሉ ችሎታ አለው፤ ፍላጎትና ችሎታ ደግሞ የአላህ ፍጡራን ናቸው።

በአንድ በኩል የሰው ስራ የራሱ የአላህ ባህሪ በመሆኑና ሰው ደግሞ የአላህ ፍጡር በመሆኑ ነው። አላህ ሱ.ወ. በተከበረው ቃሉ እንዲህ ይላል “ ከፈጣሪዎችም ሁሉ በላጭ የሆነው አላህ ላቀ” ስለዚህም የሰው ልጅ የተገኘን ነገር ማስተካከል እንጂ የሌለን ነገር ማስገኘትም ሆነ የሞተን ህያው ማድረግ አይችልም።

- 2. ተውሂድ አል-ኡሉሂያ (አምልኮታዊ ኢባዳ)

ይህ የተውሂድ ክፍል አላህ (ሱ.ወ) በአምልኮት ብቸኛ ማድረግ ነው። ሰው ከአላህ በስተቀር በአምላክ ሌላን ባለመያዝና ወደ አላህ በኢባዳ ማንንም ማቃረቢያ ሳያሻን አላህን ብቻ ጌታ አድርጎ መያዝ ግደታ ነው።

ሰዎች ይህንን የተውሂድ ክፍል በተገቢው መልኩ እንዲረዱ ነበር ታላቁ የአላህ መልእክተኛ ነብዩ (ሰዐወ) ታላቅ ትግል ያደረጉት። ሌሎችም የአላህ መልእክተኞች ይህንን መልእክት ለሰው ልጆች ለማድረስ ነበር የተላኩት። ሰዎች በተፍጥሯቸውና ፍጥረተ አለሙን በማየት “ተወሂድ ሩቡቢያን” ሊያጸድቁ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ብቻ አላህን ለማመንና ከቅጣቱ ነጻ ለመውጣት በቂ አይደለም።
ይህንን አስመልክቶ አላህ እንደዚህ ይለናል

**“... እነሆ በአላህ የሚያጋራን ሰው አላህ በርሱ ላይ ጀነትን እርም አደረገ መኖሪያውም እሳት ናት፤ ለበዳዮች ምንም ረዳት የላቸውም ...” ማኢዳ 5:72**